# የቀይ ባህር ዘንዶ!

የጐንቻው!



**ማስታወሻ**:-
*በዓረመኔው ወያኔ የግፍ አስተዳደር ተማረውና ተባረው፤በተስፋ መቁረጥ ወደ ባዕድ ሃገር በአሰቃቂ የስደት ጉዞ ላይ ሳሉ የቀባህር ማዕበል ለበላቸው አሳዛኝ ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችን መታሰቢያ ትሁንልኝ።*

የጐንቻው! 08.12.12

በየብስ በባህር አበሻን አጥምዶ፤
ውጦ የማይጠግብ መርከብ ሰው ሰርጉዶ፤
ቀይባይር አዙሪት ማህለቁን ጥዶ፤
አግዞ ጨረሰን ከቤት ምሰሷችን ከጣራችን ገምዶ፤
ካብ አጥር ሰርስሮ አገር ቤዛችንን መሰረት ጎድጉዶ፤
በአገር ሰገነት ላይ የመከራ ቋሪት ማዕበል አውርዶ፤
ቆሪጥ ያጠምቀናል እምነት፤ታሪካንችን፤ ክብራችንን ክዶ፤
እርጉም 'በላየሰብ' ደም እርም ያነገሰው 'የቀይባህር ዘንዶ'፤
**ፍጥረቱ እንደ እባብ ነው 'ወያኔው' ተወልዶ።**

በሲያል በረሃ በደደቢት ዋሻ እባብ ተቀፍቅፎ፤
ጥቁሩ ቃጥያ እየተሳሳበ ሺህ ባዶ እግር ነድፎ፤
እባብ ዘንዶ ሆነ ደም እየመጠጠ 'በሰው እርም' ገዝፎ፤
**ክብደቱ፤እርዝቱ 'አንድ ሺ ሰማኒያ' ዙሪያ ጥምጥም ታጥፎ፤**
ጅራቱ እሚጋረፍ 'አራት ኪሎ ነጥፎ'፤ ሸገር ተወንጭፎ፤
ከካቡ ወጣና ኢትዮጵያን ወረራት እልፍ ነፍስ ቀጽፎ፤
**'የእንግዴ ልጅ ቡዳ' 'በላየሰብ' እድር ዚጎቿን ጨርሶ አደረጋት ቀፎ።**

ደደብት ቢሆንም እርኩስ-ዛር-ጅራቱ፤ ሰንኮፍ፤ ማንዝላቱ፤
እነሆ ገንግኗል አገር እምብርት ላይ የዘንዶው አናቱ፤
ነፍስ እያስገበረን ሶስት ትውልድ ሲፈጅ ሃያ ሶስት ዓመቱ፤
**አላምጦ ሲተፋን ስንሽሽ፤ስንሰደድ ባራቱ ማዕዘን ስቃይ እንግልቱ፤**
ይህ ክፉ አውሬ አዚሙ፤ጠንቅ፤ መርዝ፤ ቂሙ ሲነድፍ ካፎቱ፤
**ካገር ያስመንናል፤ሞት ያስኮበልላል አለም በቃኝ ብሎ አሳሩ፤ግዞቱ፤**
**ይህ መጥፎ 'ውቃቤ' ለሰው የማይመጥን ተንኮሉ ክፋቱ፤**
ደብር አድባር ያወድማል ፈርቶ ሲፈራገጥ 'በሰራ አካላቱ'፤
አሳር እየገፋው፤ኑሮ እየገለማው፤ግዞት ሙጥኝ እንዲል ውጣቱ፤አዛውንቱ፤
**ትውልድን ይገፋል፤ በአዚሙ እየመራ፤ ለቆሪጥ ሊግብር፤ መኖ ላራዊቱ።**

በመርከብ፤በጀልባ ሺህዎች ተነባብረው ባህር፤ውቅያኖስ ከነነፍስ ሰመጡ፤
ሃገር ቤት ነስቷቸው፤ ተገፍተው፤ ተሰደው፤ ሞትን ላያመልጡ፤
**የኛማ መከራ ሃያ ዓመት በቅምጥ ቀብር የለ ለቅሶ አገር ሀዘን ብቻ እርም ሳያወጡ።**

ጊዜ ያልፋል ብለን ካገር፤ ከእርስታችን ኑረን ስንዳዳ፤
ጅምላ እያቆራኘ በቁም ይቀብረናል ከእብታችን ጓዳ፤
ኢትዮጵያን ቆፍሮ ከርስ-ምድሯን ሞላት በእስር ቤት አንጋዳ፤
ዘር ጫሪ ቆፋሪ 'የቀባህር ዘንዶ' የሺ ዘመን እዳ፤
**ወዮለት ዘንድሮ ግንቦትና ሰኔ ማዕበል ሲፈነዳ።**